ydb#B B/@éC½ B/@rsïCÂ ?ZïC KLL mNGST db#B nU¶T Uz@È

DEBUB NEGARIT GAZETA OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND

0 ፬ኛ ›mT q$_R ፯
ሀ êú ግንቦት ፳፭ qN ፪ ሺህ ዓ/ም

bdb#B B/@éC½ B/@rsïCÂ ?ZïC
KL ል E መንግሥት M ክር b@T ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 7
Hawssa, May 15, 2008

Contents

ማውጫ
አዋጅ ፳፻፳/፪ ሺህ ዓ/ም
መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን ለማስፈጸም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳፻፳/፪ ሺህ.....ገፅ 1

Proc.No 120/2000
The SNNPRS, a proclamation to excute Business process Reengineering pro.No 120/2008

አዋጅ ቁጥር ፳፻፳/፪ ሺህ ዓ/ም

መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥን ለማሰፈጸም

የወጣ አዋጅ

<u>መግቢያ</u>

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ እየተሰራባቸው ያሉ ሕጎችና የአሠራር ልምዶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት የተገኙ አዳዲስ አሰራሮችን ለመተግበር የሚያስችሉ ሆነው በመገኘታቸው፣

በክልሉ ውስጥ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ፣ ግልጽነትን የተላበሰ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በብቃት በመስጠት ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

የክልሉ መንግሥት እያስመዘገበ ያለውን አበረታች ኢኮኖሚያዊ እድገት ቀጣይነት በማረጋገጥ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሥር እንዲሰድ የሚያግዙ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር

The SNNPRS, a proclamation to execute Business process Reengineering pro.No 120/2008

Preamble

Whereas, beliving that the law and the practice that is now going on is not effective and efficient enough to implement the new result that resulted from the study on business process reengineering ;

Whereas, the region is now in need of the law that brings accountability, transparent, effective and efficient services to the public as a whole, so that the

በማስፈለጉ፣

መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ሲሆን የዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሳቦችና የሕግ የበላይነትን መሠረት እንዲያደርግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በጥናቱ የተደረሰባቸውን የአሰራር ሥርዓቶችና የአደረጃጀት ለውጦች ተግባራዊ ለማድረግ በሚል መነሻ በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎች ለመቀየር ቢታሰብ ጊዜ የሚወስድ ከመሆኑ ባሻገር በሙከራ ታይቶ ውጤታማነቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ መቀየርም አዳጋች መሆኑ ስለታመነበት፤

በ 1994 ዓ/ም በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ ‹‹በደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ማስፈጸሚያ አዋጅ ቁጥር 120/200 ዓ/ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፣

1. ‹‹ ምክር ቤት›› ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት ነው።
2. ‹‹ሕገ-መንግሥት›› ማለት በ 1994 ዓ/ም ተሻሽሎ የወጣው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሕገ-መንግስት ነው።
3. ‹‹ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ›› ማለት በክልሉ መንግሥት መ/ቤቶች ሥራን በሥራ ሂደት በማደራጀት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በተለያዩ የስራ ሂደቶች የተካሄደውን ጥናት ውጤት የሚያመለክት ሐረግ ነው።
4. ‹‹ መስተዳድር ም/ቤት ›› ማለት የደቡብ ብሔሮች ፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግስት መስተዳድር ም/ቤት ነው።
5. ‹‹ መሥሪያ ቤት ›› ማለት ቢሮ፣ ፍ/ቤት ኮሚሽን

people could get rid of poverity making a favorable condition through business process reengineering;

Whereas, a region is committed to continu in belonging sustainable development and good govenace through democratic system and which in turn needs a conductive environment to that effect;

Whereas, to implement the new law of business process reengineering in line with democratic concepts and the rule of law;

Whereas, the fact that new application of the business processing reengineering is to be implemented for pilot and this fact it is difficult to amend or repeal the laws that is now applicable in the region;

Now, therefore, in accordance with Article 51 sub Article 3(a) of the revised constitution 35/2001 of the SNNPRS, it is here by proclaimed as follws .

1. <u>Short title</u>

This proclamation may be

ጽ/ቤት፣ባለሥልጣን ተቋም፣ኤጀንሲ ወይም ማናቸውም ሌላ የክልሉ መንግሥት ቤት ነው።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት አጠናቀው ጥናቱን ተግባራዊ በሚያደርጉና በሙሉም ሆነ በከፊል በክልሉ መንግሥትበጀት በሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ላይ ብቻ ይሆናል።

4. <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልገውን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣

5. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው ጥናቱ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወይም አግባብ ባለው አካል ጸድቆ ለውጡን ሲተገብሩ በሥራ ላይ ካሉ ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር ጋር ግጭት ቢፈጠር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን ለመተግበር የወጡ ሕጎች እና በጥናት የተገኘው አዲስ አሰራር ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
2. በዚህ አዋጅ ትግበራ ሂደት የሚፈጸሙ ማናቸውም የሕግ ጥሰት በነባሩ ህግጋት መሠረት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ይሆናል።

6. <u>አዋጁ በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ የሚቆየው በክልሉ ም/ቤት ከፀደቀበት ከግንቦት 25 ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት ብቻ ነው።

7. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ከግንቦት 25/2000 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

ሀዋሣ

ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ/ም

cited as “Southern, Nations Nationalities, and peoples’ Regional state a proclamation to execute a Business processing reengineering”

2. <u>Definition</u>

Unless expressed by otherwise, in this proclamation

1. “Council” shall mean the state council of Southern Nations, Nationalities and peoples’ Region.
2. “Constitution “shall mean the 2001 revised constitution of southern Nations, Nationalities and peoples Regional State.
3. “Business process reenginerring” shal, mean a job process that organized the tasks of governmental institution so as to render accelerated and efficient services to the concerned clients.
4. “ Executive council” shall mean the state ecectutive council of the southern, nations Nationalites and peoples , Regional state,
5. “Governmental institution” shall include Bureau, Courts Commision, Office,

Institution, Agency, and any other governmental institution.

3. Scope

This proclamation is only applicable to the institution that is fully or partially run their job by the governmental budget and the business processing reenginerring study has conduted and the implemetntaiton program will commence to.

4. Power to Issue Regulation

The Executive council of the state may issue regulations necessary for the proper implementation of this proclamation.

5. Transitory proclamation

1. Any law , regulations, directives customary practices that does not go in conformity with the provisions of Business process Reengineering shall not be applicable as regard matters covered here in as of

the approval of the study conducted and this proclamation too, by the state council or by any other relevant body;

2. Any violation of laws when implementing this proclamation shall be decided according the existing previous laws.

6. Duration

This proclamation will be enforced only for two year as of its promulagation by state council.

7. Effective Date

This procalamtion shall be effected after approval of council of region from today june 2/2008 .

SHIFERAW SHIGUTE
President of the Regional state of Southern Natiions, Nationalities and peoples